# አራቱ የኤችአይቪ ደረጃዎች

በየቀኑ ለህይወት

## ደረጃ 1
## የኤችአይቪ መደላደያ ወቅት

አንድ ሰው ለኤችአይቪ ከተጋለጠ በኋላ ኤችአይቪ የሚገኝበት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማወቅ 12 ሳምንታት መጠበቅ ይኖርበታል። ምክንያቱም ሰውነታችን በደማችን ውስጥ ለገባ የኤችአይቪ ቫይረስ ምላሽ የሚሰጡ ጸረ-በሽታ ህዋሳትን ለማመንጨት 12 ሳምንታት ስለሚፈጅበት ነው። ይህ የ12 ሳምንታት ጊዜ “የኤችአይቪ መደላደያ ወቅት” ተብሎ ይጠራል።

አንድ ሰው ለኤችአይቪ ከተጋለጠ በኋላ 12 ሳምንታት ሳያልፈው ተመርምሮ ውጤቱ ኔጌቲቭ/ነጻ ቢሆን ኤችአይቪ በሰውነቱ ውስጥ ላለመኖሩ ማረጋገጫ አይሆንም። ምርመራውን በሚያደርግበት ጊዜ ለቫይረሱ ከተጋለጠ 12 ሳምንታት ሳይሞላው ስለሚችል ውጤቱ ኔጌቲቭ ከሆነ ምርመራውን እንደገና ከ12 ሳምንታት በኋላ ማከናወን አለበት።

## ደረጃ 2
## ተጓዳኝ በሽታዎች የማይታዩበት ወቅት

አንድ ሰው ለኤችአይቪ ከተጋለጠ በኋላ የመደላደያ ወቅቱም አልፎ ብዙም የበሽታ ምልክቶች ሳያሳይ ረዥም ጊዜ ሊቆይ ይችላል። ሆኖም ሰውነት በመጠኑ የመቀነስ (ከ10 በመቶ ያልበለጠ)፣ የሳምባ ምች፣ የጥፍር ላይ ፈንገስ፣ የቆዳ ሽፍታ የመሳሰሉ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ይህ ወቅት እንደግለሰቡ/ቧ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ ሊረዝም ወይም ሊያጥር ይችላል።

## ደረጃ 3
## የተጓዳኝ በሽታዎች መታያ ወቅት

የሰውነት በሽታን የመቋቋም አቅም እየተዳከመ በሄደ ቁጥር ግለሰቡ/ቧ ተጓዳኝ በሽታዎች ለሚባሉ ህመሞች ይጋለጣል። ሰውነታችን በኤችአይቪ ሲዳከም በእነዚህ ተጓዳኝ በሽታዎች በቀላሉ ይጠቃል። በስፋት ከሚታወቁት ተጓዳኝ በሽታዎች ውስጥ ቲቢ፣ የአፍ ቁስለት፣ ከአንድ ወር በላይ የሚቆይ የማያቋርጥ ተቅማጥና ትኩሳት፣ የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከዚህም በተጨማሪ ከባድ የሆነ የክብደት መቀነስ ሊያጋጥም ይችላል።

## ደረጃ 4
## የኤድስ ጠቋሚ ህመሞች መከሰቻ ወቅት

ኤችአይቪ የሰውነትን በሽታ የመከላከል ስርአት እያዳከመ ሲሄድ ኤችአይቪ የሚገኝበት ሰው ጤና ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመሄድ ወደ ኤድስ ታማሚነት ይሸጋገራል። አንድን ኤችአይቪ ያለበት ሰው የሚያጠቁ በሽታዎች ስብስብ ኤድስ ተብሎ ይጠራል። አንድ ሰው የህክምና ምርመራ ተደርጎለት የኤድስ ታማሚ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በጸረ-ኤችአይቪ ህክምና እገዛ ለብዙ አመታት መኖር ይችላል። የጸረ-ኤችአይቪ ህክምና የቫይረሱን መራባት በመቀነስ ብዙዎቹን ተጓዳኝ በሽታዎችና ህመሞች መከላከልና ማከም የሚያስችል ነው።

This Leaflet was supported by Cooperative Agreement Number PS002969 from Centers for Disease Control and Prevention (CDC). Its contents are solely the responsibility of the authors and do not necessarily represent the official views of CDC.

Betengna Listen In!

## ቤተኛ ሬድዮ ፕሮግራም

ቤተኛ ኤችአይቪ ያለባቸው ወገኖች የህይወት ተሞክሯቸውን ለህብረተሰቡ የሚያካፍሉበት የሬድዮ ፕሮግራም ነው።

- በሸገር ኤፍ.ኤም 102.1
  ዓርብ ከቀኑ 8:00
  ሰኞ ከምሽቱ 2:10 (በድጋሚ)
- ኦሮሚያ ሬድዮ እና ቴሌቪዥን ድርጅት- ኦሮሚፋ
  ቅዳሜ ከምሽቱ 12:08
  ማክሰኞ ከጠዋቱ 12:38 (በድጋሚ)
- የአማራ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት
  ቅዳሜ ከጠዋቱ 1:10
- በድምፂ ወያነ ትግራይ - በትግሪኛ
  እሁድ ከጠዋቱ 3:30
- መቐለ ኤፍ.ኤም 104.4
  ማክሰኞ ከምሽቱ 1:30
  በድጋሚ ቅዳሜ ከጠዋቱ 1:30
- ደቡብ ድምጽ ኤፍ.ኤም 100.9
  ቅዳሜ ከቀኑ 8:05
  ረቡእ ከቀኑ 8:05 (በድጋሚ)

ወገን ኤድስ ቶክላይን 952
WEGEN AIDS TALKLINE

## 952 ወገን ኤድስ ቶክላይን

«ወገን ኤድስ ቶክላይን» በኤችአይቪ/ኤድስ፣ በአባለዘር በሽታዎችና በቲቢ ዙሪያ በስልክ አማካይነት ሚስጢራዊነቱን የጠበቀ የምክርና የመረጃ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ነው

- አገልግሎቱ የሚደርሰው:- በመላው ኢትዮጵያ
- የስራ ሰአት:- ዘወትር ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:00 ሰአት እስከ ምሽቱ 2:00 ሰአት
- የስራ ቋንቋዎች:- አማርኛ፣ ኦሮሚፋ፣ ትግርኛ፣ ወላይትኛ እንዲሁም ሌሎች የ ገር ውስጥ ቋንቋዎች
- ክፍያ:- ከመደበኛ፣ ከሞባይል ወይም ከህዝብ ስልክ 952 ሲደውሉ ከክፍያ ነፃ ነዎት

Ministry of Health · PEPFAR · CDC · Johns Hopkins Bloomberg School of Public Health · Center for Communication Programs · AIDS Resource Center